**ሳምንታዊ ዜና (ሐምሌ 26 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**በመከላከያ ከፍተኛ መኮንኖች መካከል የተጀመረው ሽኩቻ ተቀጣጥሎ 3 ነባር ኮሎኔሎች ከስራ ተባረሩ፣ በመከላከያና በማረሚያ ቤት ፖሊስ ኮሚሽን ውስጥ ያሉ ነባር የሠራዊቱ አባላትን ለማባረር ዕቅድ ወጣ፣ የብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት ነባር ሰራተኞችም ሊባረሩ ነው፣ ሕዝቡ የዕለት ጉርስ ተቸግሮ ወያኔ የፕሮፓጋንዳ መሳሪያውን በብዙ ሚሊዮን ብር እየገነባ ነው፣ የመንግስት ጋዜጠኞች የግዴታ ፖለቲካ ትምህርት ሊሰጣቸው መሆኑ ተነገረ >>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>>**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ ......................**

በመከላከያ ውስጥ የተጀመረው ሽኩቻ እየተካረረ መጥቶ ሰሞኑን ከፍተኛ መኮንኖችን ማባረር የተጀመረ መሆኑን የመከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፁ::

እንደ መከላከያ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገለፃ ከሆነ ከቅርብ ቀናት ወዲህ በከፍተኛ መኮንኖቹ መካከል የተጀመረው አተካሮ ወደ ቃላት ውርወራ ተሸጋግሮ የነበረ ሲሆን፣አሁን ደግሞ ወደ ማባረር የቀጠለ መሆኑን ገልፀዋል::

በተለይም ከዚህ ቀደም በጦሩ ውስጥ፣ የአንድ ብሔር የበላይነት ነግሷል በሚልና ይህንኑ ተከትሎ ተደረገ በተባለ ግምገማ ከፍተኛ መኮንኖችን ጨምሮ በርካታ ቁጥር ያላቸው የሠራዊቱ አባሎች ከስራ የተባረሩ ሲሆን ጥቂት የማይባሉትም ቢሆን ለእስር ተዳርገው በአሁኑ ሰዓትም በታጠቅ የጦር ካምፕ ውስጥ እንደሚገኙ የገለፁት ምንጮች አሁን ደግሞ ሁኔታው አገርሽቶ በመከላከያ ሚኒስቴር ዋና መሥሪያ ቤት ውስጥ ይኸው ሽኩቻ የተጀመረ መሆኑን አብራርተዋል::

ኮሎኔል ደረሰን ጨምሮ ለጊዜው ስማቸው ያልታወቀ ሌሎች ሁለት የኮሎኔል ማዕረግ ያላቸው መኮንኖች በዚሁ ሳቢያ ከስራ የተባረሩ ሲሆን በቅርቡም እስከ ተራ ወታደር ድረስ ግምገማ በሚል በርካቶች ከስራ ሊባረሩ እንደሚችሉ ምንጮቹ ያላቸውን ስጋት ገልፀዋል::

በቅርቡ በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ በሚደረገው ግምገማ በተጨማሪ ቢ.ፒ.አር በሚል አዲስ ኮሚቴ ተዋቅሮ የአማራና የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ የጦሩ አባላትን ምክንያት እየደረደሩ ሊያባርሯቸው ስም ዝርዝር መልቀማቸውን ይኸው የውስጥ አዋቂዎች ጥቆማ ያስረዳል::

ምንም እውቀትና ትምህርት የሌላቸው የሕወሓት መኮንኖች በኮሚቴው ውስጥ የተካተቱበት ይኸው ቡድን የአይናቸው ቀለም አላማረንም ያሏቸውን በተመሳሳይ የወያኔ እስር ቤት ፖሊሶችን ለማባረር ቢ.ፒ.አር የሚል ጥናት መጀመሩም ተጋልጧል::

EthioLion.Com

የወያኔ ዋነኛ አባሎች ናቸው የተባሉት የማረሚያ ቤት ኮሚሽን አቀንቃኞች የተሰገሰጉበት ኮሚቴ ሰሞኑን ቢሮ ተሰጥቶዋቸው የሸዋሮቢት፣የቃሊቲ፣ የዝዋይና የድሬዳዋ እስር ቤት ፖሊሶችን ለማባረር ዝግጅት እየተደረገ ሲሆን፣ ከተቃዋሚ ፓርቲ ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው አለቆቻቸው በጥያቄ ምልክት ውስጥ የከተቷቸው በሙሉ ያለምንም ጥርጥር እንደሚባረሩ ምንጮቹ ገልፀው

የብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት ሰራተኞችም በዚሁ ተመሳሳይ ቢፒ. አር በሚሉት ሰንካላ መዋቅር ማስተካከያ ሳቢያ ከ30 ዓመት በላይ ያገለገሉትንና የተማሩትን ሰራተኞች ለማባረር ጥናቱ የተጠናቀቀ ሲሆን ሙሉ ብርሀን በተባለች በሕወሓት አባል የሚመራ ድርጅት መሆኑን ምንጮች ገልፀዋል::

ከአንድ ሺህ በላይ ሠራተኞች ያሉት ይኸው ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት በሀገሪቱ ውስጥ ካሉት ማተሚያ ቤቶች ቀደምትና ስመ ገናና የነበረ ሲሆን፣ በአሁን ሰዓት የድርጅቱን ሰራተኞች ለመቀነስና ለማባረር በመታሰቡ እንዲዳከም ብሎም እንዲዘጋ ለማድረግ በህወሐቷ አባል ሙሉ ብርሃን ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ቢፒ.አር. በሚል ወያኔያዊ የመዋቅር ጥናት በመቶዎች የሚቆጠሩ ነባር ሰራተኞች ለባረሩ መሆኑን ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የወያኔ ከፍተኛ መኮንኖች አስቸኳዋይ ስብሰባ ሲያደርጉ እንደነበር የመከላከያ ምንጮች ገለፁ::

በመኮንኖች አዳራሽ ውስጥ ከጠዋቱ 2:30 ሰዓት ጀምሮ እስከ 7 ሰዓት ድረስ በሳሞራ የኑስ መድረክ መሪነት የተካሄደው ይኸው የከፍተኛ መኮንኖች ስብሰባ በአሁን ወቅት በሠራዊቱ ውስጥ ስላለው ሽኩቻ እና ወደፊት ሊደረግ በሚገባው ጉዳይ ላይ ያተኮረ መሆኑን የገለፁት ምንጮች በዚሁ ስብሰባ ላይም እንደተለመደው በመከላከያ መምሪያ ውስጥ የሚገኙ ከፍተኛ የሕወሓት መኮንኖች እንደነበሩ ገልፀዋል::

በተለይም የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በቅርቡ በከፍተኛ ባለስልጣኖች ላይ ሹም ሽር ያደርጋል ተብሎ በሰፊው እየተናፈሰ ባለበት በዚህ ወቅት አስቀድሞ የጦሩን ክፍል ዝግጁ ለማድረግ የታሰበ ነው ያሉት ምንጮቹ ለብዙ ዓመታት ስርዓቱን ያገለገሉ ካድሬዎች በመሆናቸው ሲባረሩ ችግር እንዳያስከትሉ ለመቆጣጠር እንዲቻል ሳይሆን እንዳልቀረም ያላቸውን ግምት ሰንዝረዋል::

ለ8 ዓመታት በኢትዮ - ኤርትራ ድንበር ላይ ሰፍሮ የከረመው የተባበሩት ፀጥታ አስከባሪ አንሚ ከእሮብ ዕለት ጀምሮ ሙሉ በሙሉ ስራ ማቋረጡን አስታወቀ::



Ethiopia Will Prevail!

አንሚ ለ8 ዓመታት ያህል በሁለቱ ሀገራት ድንበር ላይ ሰፍሮ የድንበር አካላዩን ውሣኔ ተግባራዊ ለማድረግ ሙከራ ቢያደርግም በሁለቱ ቡድኖች መካከል ስምምነት ባለመኖሩ የተነሳ የታሰበው ያልተሳካ ከመሆኑም በላይ ሙሉ በሙሉ ስራውን አቋርጦ መነሳቱ ተውቋል::

ከሁለት ወር በፊት ምግብ፣ ነዳጅና የመሳሰሉት በኤርትራ በኩል እንዳይገባለት የተከለከለው አንሚ ጦሩን በብዛት ቀንሶ ከድንበሩ ያስወጣ ቢሆንም አሁን ግን ሙሉ በሙሉ በማስወጣቱ የተነሳ የተፈራው የሁለቱ ቡድኖች ጦርነት መቀስቀስ አይቀሬ መሆኑን ወታደራዊ ባለሙያዎች እየገለፁ ናቸው::

ወያኔ በየጦሩ ክፍል ውስጥ የተነሳውን ሽኩቻ ለማርገብና ጠንካራ ወታደራዊ ኃይል አለኝ ለማለት በቀየኑ የየጦሩን ክፍል ምስረታ እና የባንዲራ ቀን በሚል ከፍተኛ ቅስቀሳ እያደረገ ሲሆን፣ የሻዕቢያው ፕሬዝዳንት በበኩሉ የጦሩን አዛዦች በቤተ መንግስቱ ውስጥ ሰብስቦ ምስጢራዊ ውይይት ማድረጉን ገልፀዋል::

ወያኔ የተደራጀና የታጠቀ ብቁ ኃይል አለኝ እያለ ሰሞኑን በቴሌቭዥን እየወተወተ መገኘቱ ለጦርነት ዝግጁ መሆኑን የሚያመላክት ነው ያሉት እነኚሁ ለዲፕሎማቶቹ ቅርበት ያላቸው ወገኖች በተለይም በአሁን ሰዓት ወያኔ ከሕዝብ ጋር ሆድና ጀርባ በመሆኑ ውጊያ እንኩዋን ቢነሳ የህዝቡን ትኩረት ለመሳብ ሲል የአሰብን የይገባኛል ጥያቄ ተንተርሶ የሚያነሳ መሆኑንም ሳይጠቁሙ አላለፉም::

አጨብጭቦና ዘፍኖ ከቡትሮስ ቡትሮስ ጋሊ ጋር በድብቅ መክሮና ዘክሮ ለሻዕቢያ ያስረከበው ወያኔ ዛሬ በጅቡቲ ወደብ ጭማሪ ናላው ሲበጠበጥ አንጄ መኖሪያ ቤት ሌላ ጊዜ ሰፊ የእርሻ መሬት ለጅቡቲው ፕሬዝዳንት ጉርሻ እየሰጠ ቢሆንም ዘላቂ መፍትሄ ባለመሆኑና የሕዝቡንም ድጋፍ ለማግኘት ሲል ብቻ የአሰብን ጉዳይ አንስቶ ውጊያ ውስጥ መነከሩ አይቀሬ መሆኑን እነዚሁ ወገኖች ገልፀዋል::

በዚህም የተነሳ የወያኔና የሻዕቢያ ቡድኖች ጦራቸውን በተጠንቀቅ እንዲቆሙ ትዕዛዝ የሰጡ መሆኑን ለዲፕሎማቶች ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል::

በአሁን ሰዓት ወያኔ በአዲስ አደረጃጀትና አወቃቀር በሚል የፕሮፓጋንዳ ቅስቀሳ ክፍሉን አጠናክሮ ለመቀጠል የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እያስፋፋ የመጣ ሲሆን፣ በተለይም ደግሞ የመከላከያ እና የማስታወቂያ ሚኒስትርን ወጥሮ እንደያዘ ከምንጮቹ ገለፃ ለማወቅ ተችሏል::

በማስታወቂያ ሚኒስትርነት የተቀመጠው የብአዴኑ ብርሀን ኃይሉ ቢሆንም ከስሩ የቴሌቭዥንና የሬዲዮ ክፍሉን የተቆጣጠሩት የሕወሓት ካድሬዎች መሆናቸውን የገለፁት ውስጥ አዋቂዎች በየቀኑ ሠራተኞች እየለቀቁ ባዶ መስሪያ ቤት እየሆነ የመጣበት ደረጃ ላይ ደርሷል::



Ethiopia Will Prevail!

በአንድ አመት ጊዜ 3 ስራ አስኪያጆችን ያስተናገደው የቴሌቭዥን መምሪያ በቅርቡ የወይን ድመፅ ስራ አስኪያጅ የነበረውን የሕወሓት ካድሬ አምጥተው እንዲቆጣጠር የተሾመ ሲሆን፣ ለሬዲዮው ክፍልም ተመሳሳይ እርምጃ እንደተወሰደ ገልፀዋል::

በዚህም መሠረት የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የራሴ ናቸው የሚላቸውን የሕወሓት ሰዎች ቀስ በቀስ በምስጢር በማስታወቂያ ሚኒስትር ውስጥ እየሰገሰገ መሆኑን የገለፁት ምንጮች በመከላከያ ሚኒስትር ውስጥም ተመሳሳይ እርምጃ ለመውሰድ ደፋ ቀና እያለ እንደሚገኝ ታውቃል::

የመከላከያ ሚኒስቴር ሚኒስትር የነበረው ምርኮኛው የኦህዴዱ ካድሬ ኩማ ደመቅሳ ሲሆን ለአዲስ አበባ ከንቲባነት ከተሾመ በኋላ የመከላከያ ሚኒስቴርን ቦታ ባዶውን የቀረ በመሆኑ መለስ በምትኩ ታማኝ የህወሀት ሰው ለመሾም እያጠና ቢሆንም ተቃውሞ ሊያነሱ ይችላል በሚል ስጋት ለጊዜው በእንጥልጥል ላይ እንዲቆይ ያደረገው መሆኑንም ገልፀዋል::

የወያኔው ቡድን በሀገሪቱ የሚገኙ እስር ቤቶችን እያስፋፋ እንደሚገኝ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሱን ዘገባዎች ገለፁ::

የአዲስ አበባ ቃሊቲ እስር ቤት በእስረኞች በመጣበቡ ወደ ዝዋይና ሸዋሮቢት እያጓጓዘ ቢሆንም አሁንም በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ የሚገኙት እስረኞች ቁጥር እጅግ ብዙ በመሆኑ የተነሳ ቀድሞ የባህር ትራንዚት መጋዘን የነበረው እዚያው ቃሊቲ የሚገኘውን ግቢ በከፍተኛ ወጪ አዘጋጅቶ አንድ ሺህ ያህል እስረኞችን እንዳጎረበት ከደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሏል::

ወያኔ በሕዝቡ ላይ ካለው ጥላቻ የተነሳ ብቻ ከየመንገዱ ላይ እያፈሰ ለእስር የሚዳረግ መሆኑ የታወቀ ቢሆንም በአሁን ወቅት ግን ከመቼውም ጊዜ በላይ ቁጥራቸው የበዛ ዜጎች እየታሰሩ መሆኑን ከደረሰን ዘገባ ለመረዳት ተችሏል::

በቃሊቲ እስር ቤት ብቻ ከ8 ሺህ በላይ እስረኞች እንዳሉ የገለፀው ዘገባው በሸዋሮቢት፣ በዝዋይና በድሬዳዋ ደግሞ ከዚህ የዘለለ እንደሚኖር ጋር ይኸው የደረሰን ዘገባ ያስረዳል::

በሌላ ዜና የሀገሪቱ አርሶ አደሮች ማዳበሪያ እንዳያገኙ የማድረጉ ስራ በወያኔ ካድሬዎች ተጠናክሮ መቀጠሉን ከተለያዩ አካባቢዎች የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

ከዚህ ቀደም ገበሬው ሀገር በቀል በሆነ ዘዴ መሬቱን እያዳበረ ሲጠቀም የነበረ ሲሆን፣ ወያኔ በግደጅ ማዳበሪያ እንዲጠቀም እያስገደደ ካስለመደ በኋላ ዘንድሮ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ ማዳበሪያ በዱቤ እንዲሰጣቸው ቢጠይቁም በመከልከላቸው ብዙ የእርሻ መሬቶች ያለ ዘር ባዶዋቸውን መቅረታቸውን ከተለየዩ አካባቢዎች የደረሰን ዘገባ ያስረዳል::



Ethiopia Will Prevail!

ገበሬው በአሁን ሰዓት ከዕለት ጉርሱ አልፎ ለዘር የሚተርፍ እህል የሌለው በመሆኑ በአቅራቢያው በሚገኘው የግብርና ተቋማት በመሄድ ዘርና ማዳበሪያ እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ በዱቤ ይሰጠን ብለው ቢጠይቁም በመከልከላቸው ያረሱት መሬት ጦሙን ማደሩን በዚህም ምክንያት ብዙ አርሶ አደሮች ቀየአቸውን ጥለው እየተጓዙ መሆኑን አብርቷል::

ከጐንደርና ከጐጃም ገጠር ቀበሌ ያሉት እነዚሁ አርሶ አደሮች በዚሁ ችግር ምክንያት ቀየአቸውን ጥለው ወደ ከተማ የዘለቁ ሲሆን በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ ገጠሩ ባዶ ሆኖ የመቅረቱ ጉዳይ አይቀሬ መሆኑንም ይኸው የደረሰን ዘገባ ያብራራል::

የአንድ ኩንታል ማዳበሪያ ዋጋ ከ1ሺህ ብር በላይ ባናጠረበት በዚህ ወቅት የኑሮ ውድነቱ ከዕለት ወደ ዕለት እየናረ በመሄድ የዕለት ጉርስ ቀምሶ ለማዳር እጅግ ከፍተኛ ችግር የተከሰተ በመሆኑ አንዱ ሌላውን ለመርዳት በማይቻልበት ደረጃ ላይ እየተደረሰ መሆኑ ታውቋል::

ወያኔ ሕዝብ በተራበበትና የዕለት ጉርስ ቀምሶ ለማደር በተቸገረበት በዚህ ወቅት አዲስ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማድረግ በከፍተኛ ወጪ በጀት መድቦ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

በቅርቡ በአዲስ አበባ አራት ኪሎ አካባቢ ዋና ጽ/ቤቱን ለማስራትና በሰበታ ደግሞ የካድሬዎቹን ማሰልጠኛ ለማስገንባት እየተሯሯጠ ያለው ወያኔ ይህ አልበቃ ብሎ ሌላ አዲስ የቅስቀሳ ስራ ለመስራት ከፍተኛ ብር ወጪ መደረጉን አጋልጠዋል::

ለዚሁ ይረዳል የተባለው ዋነኛ መፍትሄ ሬዲዮ ፋናን በሁሉም ረገድ መገንባትና ማሣደግ ነው ብለው በማመናቸው በሬዲዮ ፋና ግቢ ውስጥ ባለ 12 ፎቅ ሕንፃ እየተገነባ ሲሆን፣ በቅርቡም የቴሌቭዥን ስርጭት ሊጀምር መሆኑን ከምንጮቹ የተገኘው ዘገባ ያስረዳል::

በብዙ ሚሊዮን ብር እየተገነባ ያለው ይኸው የወያኔ የፕሮፓጋንዳ መጠቀሚያ ሕንፃ የመጀመሪያውን የቴሌቭዥን ስርጭት በጥቅምት ወር መጀመሪያ ላይ ሊጀመር እንደሆነም ምንጮቹ አጋልጠዋል::



EthioLion.Com

EthioLion.Com